# የፖለቲካ ሀ ሁ እንዳይዛባብን

በተደጋጋሚ ሲነገር ቢባጅም ዛሬም ግልፅ አልሆን ብሎ በመገኘት ትግልን እያደናቀፈ ያለ አያሌ የተሳሳተ ዝንባሌ መኖሩን ሁላችንም እየተገነዘብን ነው:: መሰረታዊና ቀዳሚ ቢመስልም ማን ወዳጅ ማን ጠላት ለሚለው እንኳን ዛሬም፤ 14 ዓመት ወያኔን ካየነው በኋላ፤ የሕዝብ ደም ፊሶ አምባገነኑ ሲፈነድቅ ከታዘብን በኋላ የመለስ አገዛዝ የሕዝብ ዋነኛ ጠላት መሆኑን በተመለከተ  ብዥታ መኖሩ ዛሬም እየታየ ነው::

የመለስን አገዛዝ በሕዝብ ጠላትነት መፈረጅ መሰረታዊ ነው:: ይህ ካልተደረገ ትግል አቅጣጫ ያጣል፤ ይዛባል:: የወያኔን ህግ መንግስት መቀበል የሚባለውም ሊነሳ የማይችለው በዚህ መሰረት ነው:: ወያኔ ህገ መንግስት ያለውን ህገ  ወያኔ ተቀብለን በእርሱ ስር እንድንቀሳቀስ በመፈለግ ህገ  መንግሰቱን ያልተቀበለ በምርጫ አይገባም፤ ህጋዊ አይባልም ወዘተ ብሎ እገዳውን ሲጥል ቆይቷል:: የአረመኔውን አገዛዝ ህግ በቅድሚያ የሚፃረረው ራሱ ወያኔ መሆኑ ደግሞ ደጋግሞ የታየ ቢሆንም፤ ይህን ህግ አልቀበልም ማለት ቅንጦት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው:: ትግላችን ድል ሲቀዳጅ በሕዝብ ውሳኔ የሚፀድቀው ህገ መንግስት አስፈላጊዎችን አንቀፆች ማከተት የሚቻል ሲሆን የወያኔ ህገ መንግስት ግን የወያኔ ባዶ ሰነድ በመሆኑ ማንም ሊቀበለው አይገባም::

በተደጋጋሚ የመለስ አገዛዝ ለሰላምና እርቅ ጉባዔ ተጋብዞም እምቢ ያለ ኃይል በመሆኑና ድልድይ አልፎ በንፁህ ዜጋ ህይወት ላይ ግፍ የፈፀመ ኃይል በመሆኑ ሰልፉ በጠላትነት እንጂ ለእርቅ ሊሰለፍ በሚችል ኃይል ደረጃ አይደለም:: ከመለስ አገዛዝ ጋር ድርድር ከተባለ ስልጣን የሚለቅበትን መንገድ እንጂ ስልጣን ተካፋይ የሚሆንበትን ሊሆን አይችልም ማለት ነው:: ለሁሉም ጊዜ አለው ነውና ወያኔ ምናልባትም አደብ ግዘቶ፤ ክስህተቱ ተምሮና ሕዝብን ይቅርታ ጠይቆ ይጨምታል፤ ይሻሻላል የምንልበት ጊዜ አልፏል:: ዛሬ ባለው ተጨባጭ የትግል ሰልፍ የመለስ አገዛዝ ከሕዝብ ጋር በሞት ሽረት ትንቅንቅ የገባበት ነውና የዚህን ትግል አሸናፊነት ለማረጋገጥ ከመዋደቅ ፈንታ ለወያኔ ጊዜን የሚለግስ የእንደራደር ጥሪ ቦታ ሊሰጠው አይገባም:: ትግላችን የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ሳይዛነፍና ሳይደናፍ መፋፋም አለበት ማለት ነው::

ይህን ትግል ከግቡ ለማድረስ የተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት ያስፈልጋል ብለናል:: ይህ ወሳኝ ነው የተባለ የመሰባሰብ እርምጃ ግን በዘፈቀደ የሚሆን ወይም መደረግ አለበት በሚል የሚካሄድም ሊሆን አይችልም:: መለስተኛ ስምምነት ያሻዋል:: ህብረት ሊመሰርቱ የሚችሉ ኃይሎች በኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታገሉት ናቸው:: ኢትዮጵያዊ አይደለንም፤ ባዕድ ነን ወዘተ የሚሉ ኃይሎች ካሉ በዚህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ግንባር ሊሰባሰቡ የሚፈልጉም የሚችሉም አይሆኑም ማለት ነው:: በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር ለሕዝብ መብት የሚታገሉ ሁሉ በሽግግሩ ሂደት መሰረታዊ ጥያቄያቸውን ለሕዝብ ሊያቀርቡና ሊያስውሰኑም ስለሚችሉ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አካል ወይም የህብረቱ ተሳታፊ ሆነው ሊታገሉ ይችላሉ ማለት ነው:: ህብረት ስንል የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች የወያኔን አገዛዝ አስወግደው በጋራ የሽግግር መንግስት ለመመስረትና ወደ ዴሞክራሲ በሕዝብ ውሳኔና ምርጫ ለመጓዝ የሚስማሙበትን ሂደት ወይም እርምጃ ነው:: ከዚህ ውጪ የሚታየን ህብረት አልነበረም የለም፤ ሊኖርም አይችልም::

በዚህ መሰረታዊ ሀሳብ ላይ ግልፅ የሆኑ ኃይሎች መተባበር አለባቸው:: ህብረቱ ከወያኔ ለመደራደር ሳይሆን የሕዝብ ትግል መርቶ ከግብ ለማድረስ ነው:: ወያኔን ለማስወገድ ነው ማለት ነው:: ግልፅ እንሁን ስንል በእነዚህ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤያችን ከተዛባ ትግሉ ይጎዳል ብለን ስለምናምን ነው::